





# የአፄዎቹ ድርሳን

## የሳምንቱ አበይት
## የመወያያ አርስቶቻችን

---

የአፄዎቹ ራዕይ

---

ታሪካችን

---

ትግላችን

---

አንድ ለመንገድ

የአፄዎቹ ድርሳን
በሰሜን አሜሪካ ማዕከል
እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ መፅሄት
አንደኛ ዓመት ቁ. 1

መጋቢት 15 2010 ዓ.ም

# የአፄዎቹ ራዕይ

በዚህ አምድ ስር ስለ አባቶቻችን አርቆ አሳቢነት፣ ለቀጣይ ትውልዶች በክብር ስለሚተላለፈው መልካም ስራቸውና፣ ታላቅ ሃገርንና መልካም ዘርን ከታላቅ ክብርና ኩራት ጋር እንድንወርስ ያበቃን ራዕያቸው ይስተናገድበታል።

## አፄ አፄዎችን ወለደ!
## መጽሐፍ “መብረቅ መብረቅን ይወልዳል” እንዲል!

ዛሬ በዚህ አምድ ስር የሚስተናገደው የታላቋ ኢትዮጵያ ባለራዕይ መሪዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱትንና የዛሬ 150 ዓመት ገደማ በእንግሊዝ ወራሪ ሃይል በተከበቡ ጊዜ እራሳቸውን በመሰዋት መራራውን የሞት ፅዋ በጀግንነትና በክብር የጨለጡት፤ በዚህም አኩሪ ገድላቸው ወራሪውን ሃይል በማሳፈር ትውልድና ሃገርን ያኮሩትን የአፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ ድንቅ ራዕዮች መካከል አንዱን እናወሳለን። መልካም ንባብ።

አፄ ቴዎድሮስ ታላቅ ባለራዕይ ከሚያሰኛቸውና በግንባር ቀደምትነት እንዲጠቀሱ ካደረጓቸው ዘመን ተሻጋሪ ምግባሮቻቸው መካከል ተተኪ የሃገር መሪዎችንና የራዕዮቻቸው አስቀጣይ ወጣቶችን በትምህርት፣ በሃይማኖት፣ በጥበብና፣ በስነምግባር አንፆ በማሳደግና ሃላፊነት በመስጠት ተተኪን ለማፍራት የተጓዙበት ፍፁም የማይታመን እረዥም መንገድ ነው። ከሁሉም በላይ ይህን ድርጊት እንደ ተአምር ሊያስቆጥረው ከሚችሉት ምክንያቶች መካከል በጨለማው የዘመነ መሳፍንት ትውልድ መካከል የተደረገ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዚህ በ21 ክ/ዘመን ሊሞከረው ይቅርና ሊያስበው የሚደፍር የሃገር መሪም ሆነ ተራ ባለስልጣን ያለመፈጠሩ ጭምር ነው። ይህን ሃገርና ህዝብን የታደገና ዘመናትን አሻግሮ ወደ ፊት ያምዘገዘገ ድንቅ ራዕይ የታሪክ ድርሳናት እንዴት እንደዘገቡት ለአብነት ያህል አንዱን እንመልከት።

አቶ አስፋው ጀምበሩ **“አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተወለዱ ለኢትዮጵያ የተሰዉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው”** በተባለው መፅሃፍ በገጽ 4 ላይ

*“አጤ ቴዎድሮስ በመኳንንትና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን የአንድ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ካደረጉ በኋላ ቤተ መንግሥታቸውን ጎንደር አዘዞ ሎዛ ማርያም አድርገው ስለነበር*

*1ኛ. አጤ ምኒልክ ሃይለመለኮትን፣*

*2ኛ. ራስ መሸሻ ቴዎድሮስን የመጀመሪያውን ትልቁን ልጃቸውን፣*

*3ኛ. ራስ ቢትወደድ መንገሻ አትከምንና*

*4ኛ. አጤ ዩሃንስን ከሌሎች ለኢትዮጵያ ይጠቅማሉ ከሚሏቸው ወጣቶች ጋር መርጠው በጎንደር አዘዞ ተክለሃይማኖት ሲያስተምሯቸው ከቆዩ በኋላ ቤተ መንግስቱ ከጎንደር አዘዞ ሎዛ ማርያም ወደ ደብረታቦር ሲዛወር እነዚህን ተማሪዎች ዛሬ ለትምህርት ወደ አውሮፓና አሜሪካ እንደሚላከው ወደ ቋራ ማህበረ ሥላሴ ገዳም ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው እንደተመለሱ በገዳሙ መምህራን በሰጡት የብቃት ማረጋገጫ መሰረት የሚከተለው ማዕረግ ተሰጧቸዋል።*

*1ኛ. ምኒሊክ ሃይለመለኮት ደጃዝማችነት ማዕረግ*

*2ኛ. መሸሻ ቴዎድሮስ ደጃዝማችነት ማዕረግ*

*3ኛ. መንገሻ አትከምን ደጃዝማችነት ማዕረግ*

*4ኛ. ካሳ ምርጫ የባላምባራስነት ማዕረግ ተሰጧቸዋል።*

*ከገዳም አባቶችና መምህራን በተላከው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት በላምባራስ የተባሉት ካሳ ምርጫ (የኋለኛው አጤ ዩሃንስ) በተሰጣቸው ሹመት ተቀይመው ጫካ ገብተው በሽፍትነት ሲኖሩ አጤ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ተጣልተው በነበረ ጊዜ ከእንግሊዞች ጋር ውስጡን ተላልከውና ከወደብ ጀምረው በመቀበልና መንገድ በመምራትና በማስተባበር የኢትዮጵያን ምስጢር ሁሉ ለውጭ ጠላቶች በመንገር የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንዲደፈር፣ የመቀደላ ቤተ መንግሥት እንዲዘረፍና፣ ተከፋፍላ የነበረች ኢትዮጵያን አንዲት ኢትዮጵያ ያደረጓትን ታላቁንና ጀግናውን አጤ ቴዎድሮስ እራሳቸውን በእራሳቸው እንዲገድሉ አስደርገዋል” በማለት ጽፈዋል።*

ከዚህ አኩሪ ታሪክ የምንረዳውና በዘመናችን የስልጣኔና የአስተሳሰብ መለኪያ ስንመዝነው ለህሊና የሚከብድና ለማመን የሚቸግሩ ምጡቅ እሳቤዎችን ነቅሰን በማውጣት ለውይይትና ለመማማር ይረዳን ዘንድ እንመልከት።

1ኛ. በምርኮ የያዘውን የተቀናቃኙንና የባላንጣውን ልጅ ከወለዱትና ወራሽ ከሚሉት ልጃቸው ጋር እኩል በፍቅርና በጤንነት ተንከባክቦ በማሳደግ፣ በእውቀት አበልፅጎና፣ ራዕዩን አውርሶ፣ ለመንግስቱ ወራሽነት የሚያዘጋጅ የሃገር መሪ!

2ኛ. ሃገርና ህዝብን መምራት፣ መንግስታዊ ሹመትና፣ ወታደራዊ ማዕረግ በእውቀትና በችሎታ ላይ ብቻ የመሰረተ ባለራዕይ መሪ! በዘር፣ በጎሳ፣ በሃብት፣ በሃይማኖትና፣ በተለያዩ መድሏዊና ጥቅማ ጥቅማዊ ትስስሮች የሚገኝን ሃገራዊና ህዝባዊ ስልጣን ከምንጩ ያደረቀ እውነተኛ የኢትዮጵያ አባት !

3ኛ. ሃገርንና ህዝብን ከግል ስልጣን፣ ክብርና ዝና፣ እንዲሁም ቂምና ጥላቻ ነጥሎ ማየት የቻለና በተግባር የተረጎመ እውነተኛ ንጉሠ ነገሥት!

4ኛ. የሃገርና የህዝብን ቀጣይነት በእርሱ አላፊነት ያላደናቀፈ! የሚወዳትንና የሚያፈቀራትን ኢትዮጵያ ከትውልድ ትውልድ ከፍ ከፍ እንድትልለት ያለመና ለዚህም ተተኪ አፄዎችን ቀድሞ ያነፀና ያዘጋጀ ባለራዕይ አፄ! ....

በታሪካችን በደማቁ ተፅፎ የምናገኘው የአጼ ዩሐንስ 4ኛ ለሃገራቸው ሲሉ መተማ ላይ አንገታቸው በድርቡሽ ሰይፍ እስከመቀላት የደረሰውና የአጼ ምኒልክ አድዋ ድረስ መዝመትና የኢትዮጵያን አንድነት በክብር ጠብቆ ለትውልድ ማቆየት ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ አሰኝቷቸውል። በተለይም የአጼ ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርትን፣ ጠንካራ የመንግስት አስተዳደርና የተደራጀን የመከላከያ ሰራዊትን ለመገንባትና ስልጣኔን ወደ ሃገራቸው ለማስገባት ያደረጉት ጥረትና ጅማሮ በመንፈስ አባታቸው የተዘራባቸው መልካም ዘርና የተጣለባቸውን ተስፋና አደራ መልካም ፍሬ እንዳፈራ፣ የአጼው ራዕይ ማረፊያውን እንዳገኘ አስመስክረው አልፈዋል።

ዛሬ አባታችን አፄ ቴዎድሮስ በታላቅ ክብርና በፍጹም ጀግንነት ከተሰዉ ከ150 ዓመት በኋላና የአድዋን ድል በምንዘክርበት 121 ዓመት ላይ ሆነን፣ በፋሽስቱና በባንዳው የህወሃት/ወያኔ ቡድን ጨለምተኛ አካሄድ ምክንያት ሃገራችን ከገባችበት ማጥ ውስጥ ለማውጣት በየጎራው በምንታገልበት ወቅትና፣ ይልቁንም የአፄዎቹ ራዕይ ወራሾች ነን ብለን የምናምን የመንፈስ ልጆቻቸው ድርብርብ ታሪካዊ አደራ በተሸከምንበት በዚህ ፈታኝ ዘመን፤ የምንጓዝበትን መንገድም ሆነ የትግል ስልት ቆም ብሎ መገምገም፣ መዳረሻችን ማሰብና፣ አባቶቻችን የገነቡትን የታላቅነት፣ የአንድነትና፣ የስልጣኔ ፍኖት በፅናት ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ የማስረከብና ብሎም የማውረስ ግዴታችንና ሃላፊነታችን ጠንቅቀን ማወቅና በትጋት መፈጸም ይኖርብናል። ከጠላትም ጋር በምናደርገው ፈርጀ ብዙ ትግል ውስጥ አደረጃጀታችንም ሆነ የትግል ስልታችን በዚህ እሳቤና መንፈስ የተቃኘ መሆን ይኖርበታል። ይህን ታላቅ ራዕይ እንድናሳክና የትውልድ ፅኑ አደራ በብቃት እንድንወጣ የአባቶቻችን አምላክ ይርዳን!!

መብረቅ መብረቅን ይወልዳል!!!

# ታሪካችን



## ★★★ አድዋ ★★★

የሰው ልጅ ክቡር
ሰው መሆን ክቡር
ሰው ሞቷል ሰው ሊያድን
ሰውን ሲያከብር በደግነት፣ በፍቅር፣ በክብር ተጠርቶ
በክብር ይሄዳል፥
ሰው ሊኖር ሰው ሞቷል
የተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት
ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ካአጥንት
ስንት ወገን ወደቀ በነፃነት ምድር
ትናገር አድዋ፣ ትናገር ትመስክር
ትናገር አድዋ፣ ትናገር አገሬ
እንዴት እንደቆምኩኝ ከፊታችሁ ዛሬ፤
በኩራት፣ በክብር፣ በደስታ፣ በፍቅር
በድል እኖራለሁ ይኸው በቀን በቀን
ደሞ መከራውን ያን ሁሉ ሰቀቀን።
አድዋ ዛሬ ናት
አድዋ ትናንት
መቼ ተነሱና የወዳደቁት
ምስጋና ለእነሱ ለአድዋ ጀግኖች
ለዛሬ ነፃነት ላበቁኝ ወገኖች
የጥቁር ድል አምባ፣
አድዋ አፍሪካ፣
እምዬ ኢትዮጵያ ተናገሪ...
የድል ታሪክሽን አውሪ።

በእጅጋየሁ ሸባባው (ጂጂ)

# ትግላችን

## በኦሮሚያ የሚደረገው የወንድሞቻችን ግድያ ይቁም!

የዛሬ 200 ዓመት ገዳማ ልክ እንደዛሬው ታላቋ ኢትዮጵያ የ"እናት ጡት ነካሽ" በነበሩ የስልጣን ጥመኛና ጎጠኛ ልጆቿ ክፉኛ ተከፋፍላና ተዳክማ የነበረችበት ጊዜ እንደ ነበር የሃገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ሃገራት መዛግብት በአንድነት የሚስማሙበት ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ዘመን ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በስግብግብ መሳፍንትና ራሶች የጭቆና መዳፍ ስር ወድቆ ይማቅቅበት የነበረ የጨለማ ዘመን ነው፤ በዚያን ወቅት ኢትዮጵያውያን ፍትህንና ነፃነትን ፍለጋ የሚቅበዘበዙበትና የሚቃትቱበት፣ ድርቡሽና መሰል ባዕዳን ሃይሎች ደም በጠማቸው ቁጥር እንዳሻቸው ወደ መንደራችን ጎራ እያሉ ቅድስቲቱን ምድር በህፃናት አያቶቻችን ክቡር ደም የሚያጨቀዩበትና፣ ቀየውን በእሳት ቋያ ደመራ የሚያስመስሉበት አስጨናቂ ጊዜ ነበር። ይልቁንም የቀደመ ክብርና ስልጣኔዎቻችን እንደ አንድ ታላቅ ሃገርና ገናና ህዝብ ከሰቆቃና ከታሪካዊ ውርደት ሊታደጉን የማይቻላቸው ደረጃ ላይ ተደርሶ ነበር።

ታዲያ በዚህ ሁሉም ለውድቀትና ለውርደት እጅን ሰጥቶ ሞቱን በሚጠባበቅበት ዘመን ነበር፣ እትብቱን ቋራ ላይ የቀበረ፣ ትምህርቱን ማህበረስላሴ(ማብረስላሴ) ያመሰጠረና፣ ክብሩን በእንቁ የመዘነ ባለራዕይ ደቦል አንበሳ ከጎንደር ያገሳው! በዚህ ጊዜ ነበር በሌለች ኢትዮጵያ እራሱን "የኢትዮጵያ ባል" ቀይባህርን ተሻግሮ በቱርክ መዳፍ የወደቀችውን ቅድስት ሃገር "የእየሩሳሌም ውሽማ" በማድረግ ዘመናትን አሻግሮ የሚያይ ባለራዕይ የተከሰተው! የኢትዮጵያን ህዝብ ከተቀፈደደበት የጎጠኝነት አስተሳሰብና ዘረኛ አገዛዝ አውጥቶ ወደ ቀደመ አንድነቱና ታላቅነቱ ሊያመጥቀው ጎንደሬው ከቋራ ጦሩን የሰበቀው!

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ እንደ ትውልድ የተረከቧትን የተከፋፈልች ኢትዮጵያን አንድ አድርገው፣ ህዝቧን አይደለም ከድርቡሽ በአውሮጳውያን የማይደፈር ሉዓላዊነት አጎናፅፈው፣ እንዲሁም የስልጣኔና የብልፅግናን መሰረት ጥለውልንና ከክብር ሁሉ በላይ ክቡር በሆነ መስዋዕትነታቸው አስከብረውን ካለፉ እነሆ 150 ዓመታት ተቆጠሩ።

ዛሬ የአፄዎቹ ልጆች አባታችን የተወለዱበት 200ኛ ዓመት በምናስብበትና ክቡር መስዋዕትነታቸውን በምንዘክርበት 150ኛ ዘመን ላይ ሆነን ወደ ኋላ ስንመለከት፣ ከ150 ዓመታት በፊት በምን አይነት መስዋዕትነት ምን አይነት ሃገርና ህዝብ ተረከብን? ዛሬ እጃችን ላይ ምን አይነት ህዝብና እንዴት ያለች ኢትዮጵያ ትገኛለች? ነገስ ለልጆቻችንና ለቀጣዩ ትውልድ ምን አይነት ሃገርና ህዝብ ነው የምናስረክበው? ብሎ መጠየቅ፣ መመርመርና፣ ማንሰላሰል ተገቢ ይሆናል።

እርግጥ ነው በታሪካዊ ጠላቶቻችን ቀጥተኛ ድጋፍና ሴራ ሚኒሊክ ቤተመንግስት የከተመው ፋሽስቱና ባንዳው ህወሃት/ወያኔ፤ ከፍጥረቱ ጀምሮ በተለከፈበትና ዛሬም ድረስ በዋነኝነት በሚከተላቸው ኢትዮጵያን የማፍረስ፣ አማራን የማጥፋትና፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አከርካሪ የመስበር እኩይ ፋሽስታዊ አላማና ሴራ ታውሮ በየቀዬው የንጹሃን ወገኖቻችን ደም ሲያፈስ፣ ዳር ድንበር ቆርሶ በመሸጥ ሃገር ሲያሳንስና፣ አንድን ህዝብ በዘር በጎሳ ሸንሽኖ ኢትዮጵያዊነትን ሲያፈርስ 27 የሰቆቃ አመታት ተቆጠሩ።

እርግጥ ነው ህወሃትና አጋሮቹ ኦሮሞውን፣ ደቡቡን፣ ቤንሻንጉሉን፣ ጋምቤላውን፣ ... ወዘተ አደራጅተውና አስታጥቀው በአማራው ላይ የዘር ፍጅት እንዲፈጽሙ በመቀስቀስና በማነሳሳት ህልቆ መሳፍርት የሌለው የአማራ ህዝብ በጉራፈርዳ፣ በበደኖ፣ በቤንች፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ ....ወዘተ ልጅ ወልዶ ካሳደገበት ቀዬው በግፍ ተፈናቅሏል፣ በላቡ ያፈራውን ቤት ንብረቱን ተቀምቶ እንደ መፃተኛ በሃገሩ ላይ ተሳዷል፣ ማንንም ሳይበድልና በማንም ላይ እጁን ሳያነሳ በዘመነኞቹና በባለጊዜዎቹ አስከፊ ጭካኔ አካሉ ጎድሏል፣ ህይወቱን አጥቷል።

ምንም እንኳ ይህ ታላቅ ህዝብ በሃገሩ ላይ መከራና ጭንቆች ቢፈራረቁበትም ዛሬም ምላሹ ይቅርታና ለተበደሉት ጥብቅና መቆም እንደሆነ በተግባር እናያለን። ዛሬም ስለራሱ ብቻ ሳይሆን ስለወገኖቹ ፍትህና ሰላም ማግኘት ሳይታክት ይታገላል። ይጮሃል። ለዚህም አኩሪ ተጋድሎውና አርቆ አሳቢነቱ መገለጫ ይሆን ዘንድ በዚህ ርዕስ ስር አንዱን ማሳያ እናንሳ።

የጎንደር ህዝብ ትግል መነሻውና መድረሻው ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነትና፣ አንድነት ነው። ይህ የትግል ባህሪና አቋም ዛሬ ባለው ትውልድ የተጀምረ ሳይሆን በአያት ቅድመ አያቶቻችን ዘመን፤ በአፄዎቹ ዘመን የተጀመረና በክብር ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቶ እዚህ ዛሬ ያለው ትውልድ ሊደርስ ችሏል። ይህ ትውልድም የቀደምቶቹን ፈለግ በመከተልና አሁንም ውርሱን በማስፈጸም ተግቶ እየሰራ እንደሚገኝ በተግባር እያስመሰከረ ይገኛል።

## በጎዳና የሚፈሰው የኦሮሞ ወንድምና እህቶቻችን ደም የእኛም ደም ነው!

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃት ያለልኩ በሰፋለትና ባጠለቀለት የጎሳ ቀሚስ ውስጥ ገብቶ መዋኸቅና መከፋፈልን ሃብቱ ባደረገበት በዚህ አሳፋሪ ዘመንና ሁሉም የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ቡድን ያጎረሳቸውን የጥላቻ መርዝ በመቀበል በየጎጡ መሸጎ የአማራን ህዝብ በማሳደድና በመርገም 27 ዓመታትን አልፈዋል። በዚህ ወቅት ነበር የጎንደር አብዮት የተቀሰቀሰው።

የጎንደር ህዝብ ባቀጣጠለው አብዮት ይዞት ከተነሳቸው ግንባር ቀደም ጥያቄዎች መካከል "በኦሮሚያ የሚደረገው የወንድሞቻችን ግድያ ይቁም!" የሚል ነበር። ይህ ደግሞ ጎንደሬው ስለ ኦሮሞ ወገኖቹ የግፍ ግድያና ጭፍጨፋ ጥብቅና ከመቆም እኩል ሚዛን የሚደፉ መልዕክቶቹና አንድምታወች ያዘለነው። ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ቡድን ለአለፉት 27 ዓመታት የዘራውን የጥላቻ፣ የመከፋፈልና፣ የመለያየት ሴራ ከስረ መሰረቱ ያፈረሰና በፍቅር፣ በአንድነትና፣ በመተሳሰብ የተካ ነው።

2ኛ. ባንዳው ህወሃት/ወያኔ ከፋሽስት ጣሊያን የወረሰውንና ለ27 ዓመታት ተግቶ የዘመተበትን አባቶቻችን በደማቸውና በአጥንታቸው ክቡር መስዋዕትነት ያፀኑትን የአንድነት መሰረት የማፍረስ እኩይ መንገድ የገታና ወደ ቀደመው የአንድነት ጎዳና እንዲመለስ አቅጣጫ ያስያዘ አብዮት ነው።

3ኛ. ህወሃት የምኒልክን ቤተመንግስት ከረገጠ ጀምሮ በይፋ የዘመተውና የተገበረው የአማራን ህዝብ ማሳደድና በሃገሪቱ የህዝብ መገናኛ መንገዶች በይፋ ሲያሰድብና ሲያዘልፍ መኖሩ ግልፅ ነው። ይህን አማራን በይፋ የሚያሳድድና ለዘር ፍጅት የቀሰቀሰና ያመቻቸ ዘመቻ በአደባባይ ፍቅርና ይቅርታ ያሸነፈ አብዮት ነው።

4ኛ. ህወሃት እንደ ድርጅት "የአማራና የኦሮሞ ህዝብ እሳትና ጭድ ናቸው" የሚል መፈክር ያነገበና ይህን እኩይ ሃሳብ አቋሙ አድርጎ የያዘውና የህልውናውም መሰረት አድርጎ በፅኑ የሚከተለው እምነቱ መሆኑን በመሪዎቹ በኩል ደጋግሞ ለህዝብ ይፋ አድርጓል። ወያኔና እርሱ የሚመራው መንግስት ዋነኛ ተልዕኮው የአማራና የኦሮሞ ህዝብ መለያየትን ነው። ነገር ግን የጎንደር ህዝብ "በጎዳና የሚፈሰው የኦሮሞ ወንድምና እህቶቻችን ደም የእኛም ደም ነው!!" በማለት በይፋ አቋም በመውሰድና ይህን ታላቅ እምነቱን በአደባባይ በመግለጽ የህወሃትን የህልውና መሰረት ነው የናደው። በዚህም ዛሬ ድረስ በህወሃት አልሞ ተኳሾች በግፍ የሚረግፉትን የኦሮሞ ወንድምና እህቶቹን ደም እንደራሱ ደም ይቆጥራል። ጥብቅናም ይቆማል። ከሁሉም በላይ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረውንና በህወሃት ግልጽ ጫና የተፈተነውን የኦሮሞ ወገኖቹን የትውልድ ፍቅርና አንድነት አድሶበታል።

5ኛ. መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት በአንድነት ቆሞ ጠላቶቹን ሁሉ ድል አድርጎ እዚህ ትውልድ ላይ ደርሰናል። ኢትዮጵያዊው ሁሉ ይልቁንም የኦሮሞና የአማራ ነገስታት ጎንደር የጋራ ቤተመንግስታቸው፣ አድዋም የጋራ መቃብራቸው ነበር። ይህን ታሪካዊ እውነት ጥላሸት ሊቀባና ሊንድ እሩብ ክፍለዘመን ሲሰራና የጥላቻና የመለያየት ሃውልት በየመንደሩ ሲያቆም መኖር የዘመናችን ትግራይ ገዥዎች ተግባርና መታወሻ ነው። የጎንደር ህዝብ ባደረገው ህዝባዊ ሰልፍ "በጎዳና የሚፈሰው የኦሮሞ ወንድምና እህቶቻችን ደም የእኛም ደም ነው!!" "በኦሮሚያ የሚደረገው የወንድሞቻችን ግድያ ይቁም!!" እያለ በኢትዮጵያ ዳር ድንበሮች ዙሪያ በአንድነት የፈሰሰውን የአያቶቹን ደም በመዘከር ዛሬም በደሙ አንድነት ጠላት ያቆመውን ሃውልት አፍርሶታል። በዚህም የአባቶቹን አንድነት፣ ፍቅር፣ አደራና፣ ራዕይ ጠብቆ ለመጭው ትውልዶች ይተላለፍ ዘንድ ታሪኩን በደማቁ ፅፏል።

እኛም የዚህ ትውልድ አካልና የአፄዎቹ ራዕይ ወራሾች እንደመሆናቸው መጠን ዛሬም በድጋሚ ከፍ ባለ ድምፅ "በጎዳና የሚፈሰው የኦሮሞ ወንድምና እህቶቻችን ደም የእኛም ደም ነው!!" "በኦሮሚያ የሚደረገው የወንድሞቻችን ግድያ ይቁም!!" እንላለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

# አንድ ለመንገድ

## ጠንካራ እና የማይረሳ የምስጢር ቁልፍ /Password/ እንዴት ይኑረን?




በማንኛውም የቴክኖሎጂ መገልገያ ዘዴዎችና በተለይም ከኢንተርኔት ጋር ግንኙነት ያላቸው የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች አበክረው የሚመክሩንና የሚያስጠነቅቁን ጉዳይ ቢኖር የምስጢር ቁልፍ አጠቃቀምና ልንወስድ የሚገባን ጥንቃቄ ላይ ነው። ይልቁንም ህወሃትን መሰል ህዝብን በመሰለልና በማፈን የሃገሪቱን አንጡራ ሃብትና አምራች የሰው ሃይል በማባከን እንድሜውን ለማራዘም 24/7 የሚሰራ ቡድንና ዓለም ላይ የታወቁ ውድ ቴክኖሎጂዎችን በገፍ ከሚጠቀም አምባገነን ስርዓት ጋር በሚደረግ ህዝባዊ ትግል ውስጥ እንደመገኘታችን መጠን አብዝተን ልንጠነቀቅና ምስጢሮቻችን ልንጠብቅ ይገባል።

ስለሆነም በቀላሉ በጠላት የማይሰበርና የማይረሳ ጠንካራ የምስጢር ቁልፍ **/Password/** ይኖረን ዘንድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### <u>፩ኛ. የምስጢር ቁጥራችን አይነት</u>

– 12 እና ከዚያ በላይ ፊደሎችን መያዝ ይኖርበታል

– ምልክቶችን፣ ፊደሎችን እና ቁጥሮችን አዘበራርቆና ቀላቅሎ የያዘ ሊሆን ይገባል

– በመዝገበ ቃላት ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ሊይዝ አይገባውም

- የልደት ቀናችንም ሆነ የስልክ ቁጥራችን አይነት ሰዎች በቀላሉ ሊገምቷቸው የሚችሉ መረጃዎች መካተት አይኖርባችውም

- በጣም የተለመዱና በዘወትር ህይወታችን ውስጥ የምንጠቀምባቸውን ቃላት ላለመርሳት ሲባል ብቻ የምስጢር ቁጥር አድርጎ መጠቀም ሰዎች በቀላሉ አካውንታችንን ሰብረው መግባት እንዲችሉ ያደርጋል

- የሰውና የቦታ ስሞችን መጠቀም አይኖርብንም

ለምሳሌ እነዚህን ሁለት ነጥቦች በመጠቀም ጠንካራ እና የማንዘነጋው የምስጢር ቁጥር መፍጠር እንችላለን።

**ምሳሌ 1.** Kassa Hailu የተባለ ግለሰብ Kas1234 አልያም መሰል የተለመዱ የሚመስሉ የቁጥርና ፊደላት ውህድ የምስጢር ቁጥር ከመፍጠር ይልቅ Kas&Hai#23)2O የሚል ከላይ የጠቀስናቸውን ያካተተ ጠንካራ ቁልፍ መፍጠር ይችላል።

እዚህ ላይ ግን ትልቁ ችግር የሚሆነው ለማስታወስ ከባድ መሆኑ ነው። ለዚህም መፍትሄ የሚሆነው የምስጢር ኮዱን በተደጋጋሚ በማየት በአዕምሯችን እንዲታተም ለማድረግ ጥረት ማድረግ ወይም ሰዎች ሊያገኙት በማይችሉበት ሁኔታ ጽፎ ማስቀመጥ ይመከራል።

**ምሳሌ 2.** በዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅ ይኖሩበት የነበረው ህንጻ እና ዶርም ቁጥር B – 319 ቢሆን እና በየወሩ 200 ብር ወይም 10 ዶላር ከቤተሰብ ይላክልን እንደነበር እና በጣም የምንወዳት ፍቅረኛ ስም ማርታ ቢሆን B–319$10/Marta የሚል ጠንካራና የማይረሳ የምስጢር ቁጥር መፍጠር እንችላለን።

የምስጢር ቁጥራችንን ጠንካራ ማድረግ ብቻውን በቂ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ የምስጢር ቁጥር አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ተጨማሪ እርምጃዎች ልንወስድ ይገባል።

## 2ኛ. የምስጢር ቁጥር አጠቃቀምና አያያዝ

1. የምስጢር ቁጥራችንን በተለያየ ቦታ በተደጋጋሚ የምንጠቀምበት ከሆነም ሊሰራጭና ሌሎች ሰዎች በአድራሻችን ገብተው እንዳሻቸው ሊያደርጉ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።
2. ለዚህም ኢሜል አልያም እንደ ፌስቡክ ያሉ የተለያዩ ድረ ገጾችን ስንከፍት በሌላ ጊዜ የምስጢር ቁጥራችንን ማስገባት ሳያስፈልገን በቀጥታ እንዲከፍትልን የሚሰጠንን አማራጭ በአሉታ ማለፍ ያስፈልጋል።
3. ቢያንስ በየሶስት ወሩ የምስጢር ቁጥራችን በመቀያየር እራስንና ወገኖቻችንን ከአደጋ መከላከል ይቻላል።



